ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ
Nib InternationalBank

## ለንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ!

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት የተቋቋመው አስመራጭ ኮሚቴ የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ለመምረጥ የእጩ ተወዳዳሪዎችን ጥቆማ ከሰኔ 4 ቀን 2015 እስከ ጳጉሜ 3 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ብቻ ይቀበላል፡፡

በመሆኑም፣ የባንኩ ባለአክሲዮኖች ለባንካችን እድገትና መሻሻል የላቀ ውጤት ለማበርከት ብቃቱ ያላቸውንና ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ብቻ እንድትጠቁሙ ጥሪያችንን በማክበር እናቀርባለን፡፡

ለጥቆማው የሚያስፈልጉ መመዘኛዎች ሰኔ 4 በአዲስ ዘመን፣ ሰኔ 4፣ ሐምሌ 2፣ ነሐሴ 7 እና 14 በሪፖርተር እንዲሁም ሰኔ 3 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አድማስ ጋዜጣ እትም መመልከት የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናስታውቃለን፡፡

## ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚያስፈልጉ መመዘኛዎች፡-

1. የባንኩ ባለአክሲዮን የሆነ፣
2. በዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ፣
3. ዕድሜው 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣
4. ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ወይም ከታወቀ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያለው፣
5. በባንኪንግ፣ ፋይናንስ፣ አካውንቲንግ፣ ማኔጅመንት፣ ኢኮኖሚክስ፣ ህግ፣ ቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን፣ ኢንቨስትመንት ማኔጅመንት፣ ኦዲቲንግ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የትምህርት ዝግጅትና አግባብነት ያለው የሙያ ልምድ ያለው ቢሆን ይመረጣል፣
6. በሌላ የፋይናንስ ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ያልሆነ፣
7. ሀቀኛ፣ ታማኝ፣ ጠንቃቃ፣ ጠንካራ ሠራተኛ እና መልካም ስነ-ምግባር ያለው፣
8. በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል፣ ትክክለኛ ያልሆነ የሂሳብ መግለጫ በማቅረብና በመሳሰሉት ተከስሶ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት የማያውቅ፣
9. በቂ ገንዘብ ሳይኖረው ቼክ ሰጥቶ ሂሣቡ ያልተዘጋበት፣
10. ከመመረጡ በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በሌላ ሀገር በንግድ ማኅበር አደራጅነት፣ ዳይሬክተርነት፣ ሥራ አስኪያጅነት፣ ተቆጣጣሪነት፣ ኦዲተርነት ወይም በሌሎች የሥራ ኃላፊነቶች ሲሠራ በእምነት ማጉደል፣ በስርቆት፣ በማጭበርበር ወንጀል ጥፋተኛ ያልተባለ፣
11. በራሱ ወይም በሚመራው ድርጅት ላይ የመክሰር ውሳኔ ያልተሰጠበት፣ በኪሳራ ምክንያት ንብረቱ ለዕዳ ማቻቻያነት ያልተወሰደበት፣

12. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ በሐራጅ ያልተሸጠ፣ ተከስሶ ያልተፈረደበት ወይም የቦርድ ዳይሬክተር፣ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም የበላይ ኃላፊ በመሆን የሚመራው ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈሉ ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ የብድር ደረጃ ያልዞረበት ወይም ያልገባበት፣

**ማሳሰቢያ፡-**

1. በተባዕታይ ጾታ የተገለጸው ለአንስታይ ጾታም ያገለግላል፡፡
2. መስፈርቱን የሚያሟሉ ሴት ዕጩዎች ይበረታታሉ፡፡
3. ጥቆማው በውክልና የቀረበ ከሆነ ውክልናው ጥቆማውን ለማቅረብ የሚያስችል ሆኖ የውክልና ፎቶ ኮፒው ከመጠቆሚያው ቅፅ ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
4. ጠቋሚው ባለአክሲዮን ግለሰብ/ማኅበር ወይም ድርጅት የተጠቋሚውን ፈቃደኝነት አስቀድሞ ማረጋገጥ አለበት፡፡
5. የመጠቆሚያውን ቅፅ የኮሚቴው ጽ/ቤት ከሚገኝበት ከንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ዋናው መ/ቤት 22ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 10 እና ከባንኩ ቅርንጫፎች ወይም ከባንኩ ድረ-ገጽ www.nibbanksc.com ማግኘት ይቻላል፡፡
6. ለጥያቄና ማብራሪያ በኮሚቴው ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ ወይም በኮሚቴው ጽ/ቤት ስልክ ቁጥር 0118963628 ወይም 0115541132 በመደወል መጠየቅ ይቻላል፡፡
7. የመጠቆሚያ ቅፁ በአግባቡ ተሞልቶና ተፈርሞበት፣ ማኅበር/ድርጅት ከሆነ ደግሞ ማኅተም ተደርጎበት በባንኩ ዋና መ/ቤት 22ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 10 ወይም በባንኩ ሁሉም ቅርንጫፎች በአካል በመቅረብ ማስረከብ ወይም በባንኩ ፖስታ ሳጥን ቁጥር 2439 መላክ ይቻላል፡፡
8. ጥቆማ ማቅረብ የሚቻለው እስከ ጳጉሜ 3 ቀን 2015 ዓ.ም. 11፡00 ሰዓት ድረስ ነው፡፡
9. ከጳጉሜ 3 ቀን 2015 ዓ.ም. በኋላ የሚቀርቡም ሆነ የሚደርሱ ጥቆማዎች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

**የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አክስዮን ማኅበር**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ**